# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ዘመነ ጽጌ፣ ከመስከረም ፳፮ እስከ ህዳር ፮ ቀን ድረስ ያለው ዘመነ ጽጌ ይባላል።

## የዕለቱ ምስባክ

ፍሬ ጸማከ ተሴሠይ
ብፁዕ አንተ ወሠናይ ለከ
ብዕሲትከ ከመ ወይን ስሙር ውስተ ጽርሐ ቤትከ

የድካም ፍሬን ትመገባለህ
ምስጉን ነህ መልካምም ይሆንልሃል
ሚስትህ በቤትህ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት

መዝ ፩፻፳፯፥፪

ወይም

እስመ ፈተወ ንጉሥ ስነኪ
እስመ ውእቱ እግዚእኪ
ወይሰግዳ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ

ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና
እርሱ ጌታሽ ነውና
የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻውን ይዘው ይሰግዱለታል።

መዝ ፵፬፥፲፩

ወንጌል፥ ዮሐ ፫፥፳፭ እስከ ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ ጐሥዐ (ቅዳሴ ማርያም)

## የዕለቱ ትምህርት

### «ሙሽራ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው»

ዮሐ ፫፥፳፱

ራሱን በሙሽራውና በሙሽራይቱ ኅብረት በተደሰተና ዓላማውም ሙሽራይቱን ከሙሽራዋ ጋር ማዋሃድ ሁለቱን አንድ አካል ማድረግ በሆነ እንዲሁም ለዚህ ዓላማው ተስማሚ በሆነ ስም ራሱን «ሚዜ» ብሎ የሚጠራው መጥምቀ መለኮት ከአይሁድ ደቀ መዛሙርት ለቀረበለት ጥያቄ መልስ የሰጠው የምሳሌና ቅኔ ቃል ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ በተደጋጋሚ የተመሰሉበት ምሳሌ የተጠሩበት ስም ቢኖር ሙሽራና ሙሽሪት የሚሉት ቃላት ናቸው። ሙሽራ የሚባለው በልዩ ልብስ አጊጦ በብዙ ሰዎችና በሚዜዎቹ ታጅቦ የሚታይ በቤቱም ብዙዎችን የሚመግብ ድግስ ያዘጋጀ ነው። ይህንም በጌታችን ትምህርትና ምሳሌ እናውቃለን (ማቴ ፳፭፥፩-፲ ። ዮሐ ፪፥፱)።

ይህ ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዮሐንስ እንደተናገረ «ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ [ኢየሱስ] ሙሽራ ነው። መድኃኒታችንም ራሱን በሙሽራ ሐዋርያትን በሚዜ መስሎ ተናግሮአል (ማቴ ፱፥፲፭ ። ማቴ ፳፭፥፩-፲) ሙሽራይቱ ደግሞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት። በትንቢት «… ሙሽራው በሙሽራይቱ ደስ እንደሚለው እንዲሁ አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል።» (ኢሳ ፷፪፥፭) እንደተባለላት ፊታ (ጋለሞታ) ያልሆነችው ድንግል የሆነችው ሙሽሪት በጽድቅና በቅድስና በቅዱሳን

ዘመነ ጽጌ፣ ከመስከረም ፳፮ እስከ ህዳር ፮ ቀን ድረስ ያለው ዘመነ ጽጌ ይባላል። በዘመነ ጽጌ በሙሽራውና በሙሽራይቱ ምሳሌ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ በጽጌ (በአበባ) መነጋገራቸውን መኃልየ መኃልይ የተዘመረ ይታሰብበታል። እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕጻኑን ኢየሱስን ይዛ ወደ ግብጽ መሰደዷን፣ በስደትም ከሕጻኑ ጋር ብዙ መከራ መቀበሏን በሕጻኑም ስደት የግብጽ ጣዖታት መሻራቸውን፣ ሰይጣንም ከሰው ልቡና መሰደዱን፣ ክርስቶስም ተስፋ ስዱዳን መሆኑን «ኢየሱስ ስዱድ ተስፋሆሙ ለስዱዳን» እያለች በመዘመር ታሳስባለች።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ርዕስ ትዌድሶ መርዓት
ሙሽራይቱ (ቤተ ክርስቲያን) ሙሽራውን
(ኢየሱስን) ታመሰግነዋለች።

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ኤፌ ፭፥፳፩ - ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ራዕይ ፳፩፥፩-፱ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፩፥፴፩ - ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

የጌጥ ልብሶች ራስዋን ያስዋበች ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ናት (ራዕ ፳፩፥፱ ። ራዕ ፳፪፥፲፯)።

ለምእመናን ከተዘጋጀችው መንግሥት ሰማያት ጋር በሙሽርነትዋ ውበት የምትወዳደረው (ራዕ ፳፩፥፩-፱) ጌጧና ውበቷን የማትረሳ (ያውም ፈጣሪዋ ነው።) ቅድስት ቤተ ክርስቲያን (ማኅበረ ምእመናን) ናት። ይህችን ሙሽራ በተመለከተ የተሰበከው ምስባክ በትርጉሜ ዳዊት በወንጌልህ በጽድቅህ የነገሡ ምእመናን እና የምእመናን (ነገሥታት) ልጆች ለጌትነትህ ይገዛሉ፤ ንጉሥ ክርስቶስ ውበትሽን (በጐ ምግባር ሃይማኖትሽን) ወዷልና እርሱም በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ (በመስቀሉ በወንጌሉ) የፈጠረሽ ጌታሽ ነው የሚል ምስጢር ያዘለ ነው።

በገባሬ ሰናዩ ዲያቆን የተነበበው (ኤፌ ፭፥፳፩ እስከ ፍጻሜው) በተጠቀሰው መልእክትም ክርስቶስን በሙሽራ ቤተ ክርስቲያን በሙሽሪት መስሎ ጠቅሷቸዋል። ክርስቶስ ባል ለሚስቱ እንደሚሞት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሞቷል፤ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ደሙንም በማፍሰስ ቀድሷታል፤ አሁንም ቢሆን ከክርስቶስ ውጪ ባዕዳንን የወሸመች አመንዝራ ሴት እንዳትሆን መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን ይመክሯታል። ባል ያለት ሚስት በባሏ የታሰረች እንደሆነች ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ውጪ ብትሄድ በመዓት ትቀጣለች (ሮሜ ፯፥፪)።

በብሉይ ኪዳን በዝሙት የሚገኙ የሞት ፍርድ ይፈረድባቸው እንደነበር (ዘሌ ፳፥፲) ዛሬም ክርስቶስን የተወ ቢኖሩ ከሌላም ጋር በጣዖት ሥራ ቢተባበሩ ሕጉንም ቢጥሉ ጌታ የሚፈረድባቸው የፍዳ ሰዎች ናቸው (ኤር ፱፥፫ ። ማቴ ፲፪፥፴፱)

እግዚአብሔር ከዚህ ይሰውረን።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር … አሜን።